- ድርጅቱ ለሕትመቱ የመደበው የካፒታል መጠን፣
- የሕትመቱ ይዘት (በማመልከቻ ቅጽ ከተዘረዘሩት አንዱን ብቻ በመምረጥ ምልክት ማድረግ)፣
- ከድርጅቱ አባላት መካከል ቁጥሩ ከመቶ ሺህ በላይ የሆነ ነዋሪ ካለበት አካባቢ የብሮድካስት ወይም በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት ከያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያለው ሰው ካለ በቅጹ ላይ ይገለጻል፣
- ከአመልካች ድርጅት እንዲሁም ከድርጅቱ አባላት ጋር የቅርብ ግንኙነት ማለትም ለአመልካች ድርጅት እርዳታም ሆነ ስጦታ የሰጠ ወደፊትም ለመስጠት ቃል የገባ ወይም ከአባላቱ ጋር የቅርብ ዝምድና ያላቸው ሆነው ቁጥሩ ከአንድ መቶ ሺህ በላይ ነዋሪ የሆነ ካለበት አካባቢ የብሮድካስት አገልግሎት ፈቃድ ወይም በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት ከያዘ ኩባንያ ካፒታል ወይም አክስዮን በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ውጤታማ ቁጥጥር ያላቸው ግለሰቦች ካሉ ይጠቀሳሉ፣
- የሕትመቱ ዓይነት (ጋዜጣና መጽሔት)፣
- የሕትመቱ ስም (አመልካቹ ስያሜ በሌላ ሰው አለመያዙን በስልክ ወይም በባለሥልጣን መ/ቤቱ በአካል በመገኘት በቅድሚያ ማጣራት ይኖርበታል)፣
- ሕትመቱ የሚሰራጭበት ቋንቋ፣ ክልል እና የሚሰራጨበት ጊዜ ግልጽ በሆነና ስርዝ ድልዝ በሌለው መልኩ መሞላት አለባቸው፡፡



## በየጊዜው የሚወጣ የሕትመት ውጤት እና የዜና አገልግሎት ምዝገባ የት ይካሄዳል?

ምዝገባው የሚካሄደው በባለሥልጣን መ/ቤቱ ቢሮ ቁጥር 204 በአካል በመቅረብ ወይም ከተቋሙ ድረ-ገጽ www.eba.gov.et በመጎብኘትና ለምዝገባው የተዘጋጀውን ቅጽ በመሙላት ከላይ በተጠቀሰው ቢሮ ይዞ በመቅረብ ምዝገባውን ማካሄድ ይችላሉ፡፡

በዘርፉ መሰማራት የሚፈልጉ አካላት ከባለሥልጣኑ የሚሰጠውን የምዝገባ የምስክር ወረቀት ማግኘት ይገባቸዋል፡፡




*በስራ ላይ ከሚገኙ የህትመት ውጤቶች በጥቂቱ*



**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

The Federal Democratic Republic of Ethiopia

**የኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን**

Ethiopian Broadcasting Authority

# በየጊዜው የሚወጣ የሕትመት ምዝገባ እንዴት ይካሄዳል?

## አድራሻ


ስልክ/Tel: 251-0115538759/60

ፋክስ/Fax: 251-0115536750

ኢሜይል/Email:e.b.a1@ethionet.et

ድረ-ገጽ/Website: WWW.eba.gov.et

የመ.ሣ.ቁ/P.O.Box 43142

# መግቢያ

ዜጎች በሕገ መንግስቱ አንቀጽ 29 የተደነገገውን ሐሳብን በነፃነት የመግለጽ መብት ተግባራዊ ከሚያደርጉባቸው የመገናኛ ብዙኃን ዘርፍ አንዱ የሕትመት ውጤት ነው፡፡ ይህ ዘርፍ በሚፈለገው መጠን እንዲያድግና የዜጎች የሐሳብ መንሸራሸሪያ መድረክ እንዲሆን የሚያስችል የሕግ ከለላ ተሰጥቶት በአገራችን ዘርፉ እየተስፋፋ ይገኛል፡፡

ከዚህ አንጻር ቀደም ብሎ በማስታወቂያ ሚኒስቴር ይሰራ የነበረው የሕትመት ፈጉሳቶቱ ሥራ የመንግስት ኮሙኒኬሽንን ጉዳዮች ጽ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው ደንብ ቁጥር 158/2001 አንቀጽ 11/1/ ላይ ለኢትዮጵያ ብሮድካስት ባለሥልጣን ተሰጥቷል፡፡

ባለሥልጣን መ/ቤቱ ከየካቲት ወር 2001 ዓ.ም. ጀምሮ በየጊዜው የሚወጡ የሕትመት ውጤቶችና የዜና አገልግሎት ምዝገባ የጀመረ ሲሆን እስከ ኅዳር ወር 2004 ዓ/ም ድረስ 211 ለሚሆኑ ከአንድ ክልል በላይ ለሚሰራጩ በየጊዜው የሚወጡ የሕትመት ውጤቶች የምዝገባ ሥራ አከናውኗል፡፡ ከዚህ ውስጥ 83ቱ ጋዜጦች ሲሆኑ ቀሪው 128 ደግሞ መጽሔቶች ናቸው፡፡

ሆኖም ግን በአገልግሎቱ ዙሪያ ለተገልጋዮች ማብራሪያ ማዘጋጀት በማስፈለጉ የሕትመት ሥራ እና የዜና አገልግሎት ምዝገባን በተመለከተ ለተገልጋዮች ይጠቅማሉ የምንላቸውን መረጃዎች በሚከተለው መልኩ አዘጋጅተናል፡፡



## “በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት” ምን ማለት ነው?

በየጊዜው የሚወጣ ሕትመት ማለት አንድ ቋሚ ስያሜ በመያዝ በተወሰነ የጊዜ ክፍተት ሳይቋረጥ በተከታታይ እንዲወጣ ታቅዶ ቢያንስ በዓመት ሁለት ጊዜ የሚታተም አጠቃላይ ስርጭት ያለውና በጠቅላላው ሕብረተሰብ ወይም በአንድ በተወሰነ የሕዝብ ክፍል እንዲነበብ ታስቦ የሚሰራጭ ጋዜጦችንና መጽሔቶችን የሚያካትት የሕትመት ሥራ ነው፡፡

- በውልና ማስረጃ የጸደቀ የማኅበሩን መተዳደሪያ

## አመልካች ከማመልከቻው ጋር አባሪ አድርጎ የሚያቀርባቸው ማስረጃዎች ምንድን ናቸው?

ደንብና መመስረቻ ጽሑፍ ዋናውንና ፎቶ ኮፒ ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣

- የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት ዋናውንና ፎቶ ኮፒ፣
- የማኅበሩ አባላት የታደሰ የነዋሪነት መታወቂያ ወይም ፓስፖርት፣
- የሕትመቱ ስምና አርማ በA4 Size በሆነ ወረቀት ዋናውንና ፎቶ ኮፒውን ማቅረብ ይኖርባቸዋል፣ (ለሁሉም ማስረጃዎች ኮፒዎች ሲኖራቸው ይገባል)



## የማመልከቻ ቅጹ እንዴት ይሞላል?

- ቅጹ የሚሞላው በድርጅቱ ዋና ሥራ አስኪያጅ ወይም ሕጋዊ ተወካይ ነው፣
- በመገናኛ ብዙኃንና መረጃ ነፃነት አዋጅ ቁጥር 590/2000 አንቀጽ 9 ንዑስ አንቀጽ 3 የተቀመጠውን መሠረት በማድረግ አመልካች ድርጅቶች በማመልከቻ ቅጹ ላይ አሳታሚውን ወይም የዜና አገልግሎት ድርጅቱን ስምና አድራሻ እንዲሁም ቅርንጫፍ ጽ/ቤቱን ይገልጻሉ፣
- በየጊዜው የሚወጣው ሕትመት ወይም ዜና አገልግሎት ላይ በአሳታሚው ወይም በዜና አገልግሎት ድርጅቱ ከ2 በላይ የበለጠ አክስዩን ድርሻ ያላቸውን ሰዎች ስም፣ አድራሻ፣ ዜግነትና የአክስዮን መጠን መግለጽ አለበት፣